ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)


ሚያዚያ 21፣ 2004ዓም

**አስቸኳይ መግለጫ፡-**

# ለእስልምና፣ ክርስትና፣ ይሁዲ እምነት ተከታዮችና ለመላው የሃይማኖት ነጻነት አፍቃሪዎች፤

**ቢስሚላሂ ረህማኒ ረሂም፤ በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ በሆነው ሳላም፤**
**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ፤ የክርስቶስ ሰላም ይብዛላችሁ፤**
**የአብርሃም፣ የይስሃቅ፣ የያዕቆብ አምላክ በሆነው አዶናይ ስም ሻሎም፤**
**የሃይማኖት ነጻነት አፍቃሪ ለሆናችሁ በሙሉ ሰላም ለእናንተ ይሁን፡፡**

ይህንን አስቸኳይ መግለጫ የሚደርሳችሁ የእምነት ተከታዮችና ሰላም ወዳዶች በሙሉ በአሁኑ ጊዜ በሙስሊም ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለውን አስቸጋሪ ጉዳይ በተመለከተ አብራችሁ እንድትቆሙ እየጠየቅን በአጠቃላይ ደግሞ ያለ አንዳች ጣልቃገብነት በነጻነት እምነቱን እንዳያከብር ችግር ላይ ከወደቀው ሕዝባችን ጋር አጋር እንድትሆኑ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) በኢትዮጵያ ከዚያም ሲያልፍ በአፍሪካ ቀንድ የማኅበራዊ ፍትህ ይሰፍን ዘንድ የሚታገል ድርጅት እንደመሆኑ የሃይማኖትን ነጻነት በሚቃወም መልኩ በክርስትያኖች ላይ እየደረሰ ያለውን ሰቆቃ አጥብቆ የሚቃወም ሲሆን አሁን ደግሞ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በሙስሊሙ ወገናችን ላይ እያደረሰ ያለውን የመከፋፈልና የሃይማኖት መብትን የመግፈፍ ተግባር የዓለም ኅብረተሰብ እንዲያውቀውና ከማውገዝ ባለፈ መልኩ ከሙስሊሙ ሙዕሚን ጋር እንዲቆም ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡ እያንዳንዳችን ለሁላችን ካልቆምን በስተቀር የእኛም ነጻነት ዋስትና የለውም - **“ሁላችንም ነጻ ካልወጣን ማንም ብቻውን ነጻ ሊሆን አይችልምና”**፡፡

ውስጥ የሚገኙት ሁሉ መብታቸው እንዲከበር በኅብረት ካልቆምንና ካልታገልን በስተቀር አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመመሥረት ቀርቶ ለማሰብም እንኳን አንችልም፡፡ በመሆኑም እያንዳንዳችን ለራሳችን እንዲጠበቁልን የምንፈልጋቸውን የሃይማኖትንም ሆነ የአመለካከት መብቶች በምንም ዓይነት መልኩ በሌሎች ላይ እንደ ቀንበር በመጫን ከፈጣሪ የተሰጡ በማንም ሊገሰሱ የማይችሉ መብቶችን መንፈግ አንችልም፡፡ የራሳችን መብት የሚከበረው የሌሎችን ስናከብር ነው፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ ከማንኛውም የሃይማኖት፣ የዘር፣ የአመለካከት፣ የጾታ፣ የቋንቋ፣ የፖለቲካ፣ የሃብት፣ ወዘተ ልዩነት በፊት ሰብዓዊነትን ስናስቀድም ለሌላው መቆም እንችላለን - **“ከዘረኝነት ይልቅ ሰብዓዊነትን ማስቀደም”** ማለትም ይኸው ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በአገራችን የሚገኙትን ሃይማኖቶች በሙሉ ቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ በያዘው አጀንዳ መሠረት በየእምነቱ ውስጥ የሚያካሂደው የመከፋፈልና የማበጣበጥ ተግባር ከብዙዎቻችን የተሰወረ አይደለም፡፡ በየእምነቱ የሚገኙ ሁሉ በኅብረት በሰላም የአምልኮ ተግባራቸውን በሚወጡበት ጊዜ ለህወሃት/ኢህአዴግ እንቅልፍ የሚነሳው በመሆኑ በመጀመሪያ በምዕመናኑ መካከል መበጣበጥ ከፈጠረ በኋላ ክፍፍል በሚነሳበት ጊዜ ደግሞ አስታራቂ መስሎ እምነቱን ለመቆጣጠር የራሱን ሰዎች ለማስቀመጥ ዕድሉን ያመቻቻል፡፡ በአገራችን ታላላቅ የሚባሉት ዕምነት ተከታዮች ለዘመናት ተከባብረውና ተፈቃቅረው መኖራቸው ለአቶ መለስ አገዛዝ ችግር የፈጠረ በመሆኑ በየቦታው የግጭትና የመከፋፈልን እሣት እየጫረ፤ አሸባሪነትን እዋጋለሁ እያለ ራሱ ግን የአሸባሪነትን ሥራ እየሰራ ይገኛል፡፡ አሁን ደግሞ በተለይ በሙስሊሙ ሙእሚን ዘንድ የቆሰቆሰው ጠብ ከቁጥጥር ውጪ እየሆነ በመምጣቱ ይህንን የአስቸኳይ ጊዜ መግለጫ አውጥተናል፡፡



ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ለጋራ ንቅናቄያችን መልዕክት በመላክ አገዛዙ በሃይማኖታቸው ላይ እያደረሰ ያለውን ካሳወቁን ጊዜ ጀምሮ ሁኔታውን በቅርበት ስንከታተል ቆይተናል፡፡ በመሆኑም የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት አመራረጥን በመቆጣጠር የሙስሊሙ ኅብረተሰብ ውክልና የሌላቸውን የመጅሊስ ኃላፊዎችን በመሾም፣ መሠረታዊ የሃይማኖት ነጻነታቸውን በመቆጣጠር፣ የማምለኪያ ሥፍራዎቻቸውን በማፍረስ፣ የመቻቻል አቋም ያላቸውን ሙስሊም ምሁራን በሙዕሚኑ ላይ ተጽዕኖ እንዳይኖራቸው በማድረግ፣ የሃይማኖት ት/ቤቶችንና ኮሌጆችን በመዝጋት፣ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን "አህባሽ" በተሰኘ እንዲሁም ከሊባኖስና ሶሪያ በመጡ ጽንፈኛና ባዕድ አስተምህሮቶች ለማጥመቅ የሚያደርገው ከብዙው ጥቂቱ ነው፡፡ (ለአቶ መለስ የጻፉት ደብዳቤ እዚህ ላይ ይገኛል፡፡ (http://www.solidaritymovement.org/amharic/120424-pm.pdf) እንዲሁም የኢትዮ/አሜሪካ ሙስሊም ጊዜያዊ ኮሚቴ በህዳር ወር ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር በጻፈው ደብዳቤ ላይ አቋሙን ሲገልጽ "**የሃይማኖትንና የፖለቲካ ጽንፈኝነትን እንቃወማለን፤ ለሰላም ዋንኛው መንገድ ፍትሕ መሆኑን እናምናለን፤ ከማንኛውም ዘር፣ ጎሣና ሃይማኖት ውጪ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን በመሆኗ . . .**" የአቶ መለስ አገዛዝ "**ለየትኛውም ሃይማኖት ሳይወግን ሁሉንም በእኩል ዓይን**" እንዲመለከት የውጭ ጉዳይ መ/ቤቱ በኢትዮጵያ በሥልጣን ላይ በሚገኘው አገዛዝ ላይ ተጽዕኖ እንዲያደርግ ጠይቀዋል፡፡ የደብዳቤው ሙሉ ቃል እዚህ ላይ ይገኛል (http://www.solidaritymovement.org/downloads/120424-Letter-to-State-Dept.pdf)

በአሁኑ ጊዜ የሙስሊሙ ኅብረተሰብ እያነሳ ያለው መሠረታዊ ጥያቄዎች፡-

1. **የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በእስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት (መጅሊስ) ላይ ያለውን ጣልቃገብነት እንዲያነሳ፤**
   በኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮችን በተመለከተ ሥልጣን ያለው የእስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት አመራሮች በየሦስት ዓመቱ በኢትዮጵያ ከሚገኙ ኢማሞች የሙስሊሙን ኅብረተሰብ በሚወክል መልኩ እንደሚመረጡ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ከስድስት ዓመት በፊት ህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በቤተክህነት እንዳደረገው ሁሉ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ለዘመናት ሲለማመዱት በቆዩት በዚህ ውክልና ባለው ሂደት ላይ ጣልቃ በመግባት ምርጫ ሳይካሄድ ውክልና የሌላቸውና ለህወሃት በታማኝነት የሚቆሙ ግለሰቦችን የመጅሊስ አመራር አድርጎ ሾሟል፡፡ በውጤቱም በመላው ኢትዮጵያ በሚገኙ በመስጊዶች ላይ የእጅ አዙር ቁጥጥር እንዲኖረው ለማድረግ ችሏል፡፡ ከሦስት ዓመት በኋላም ህወሃት/ኢህአዴግ የመጅሊሱን አመራሮች ሥልጣን ያለምንም ምርጫ እንዲቀጥል ያደረገ ሲሆን እነዚህ አመራሮች በሚዘዋወሩበት ቦታ ሁሉ የታጠቁ የደኅንነት ሰዎች እንደሚያጅቧቸው ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ ይህ በህወሃት የተጠለፈ አመራር በኢትዮጵያ ከተስፋፋው የዘር ፖለቲካ መካከል አንዱ በመሆን በአገራችን ላይ ያለውን የአፈና ሥራ በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ በተለይ በአሁኑ ወቅት አዲስ የመጅሊስ አመራሮች የሚመረጡበት ጊዜ በመሆኑ ሙስሊሞች ዝም አንልም በማለት ነጻነታቸውን በተግባር ለመተርጎም በመነሳታቸው ውጥረቱ ሊጨምር ችሏል፡፡

2. **ጽንፈኛና ባዕድ የሆኑ አስተምህሮቶችን ከማስፋፋት ዘመቻ ህወሃት/ኢህአዴግ እንዲታቀብ፤**
   በኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት ውስጥ ተሰይመው የሚገኙ እነዚህ "አስመሳይ ሙስሊሞች" ያላቸውን ሥልጣን በመጠቀም ለኢትዮጵያ ሙስሊሞች ባዕድና ጽንፈኛ በመሆኑ በበርካታው የሙስሊም ኅብረተሰብ የተወገዘውን **የአህባሽ አስተምህሮት** እያስፋፉ ይገኛሉ፡፡ ይህንን የተቃወሙ ሁሉ ደግሞ እንግልት፣ እስራት፣ ከሥራ መባረር፣ ወዘተ እየደረሰባቸው ይገኛል፡፡ በአንድ በኩል አሸባሪነትንና አክራሪነትን እዋጋለሁ እያለ ለዓለምአቀፉ ኅብረተሰብ ቀን ከሌት የሚወተውተው ህወሃት በሌላ መልኩ ደግሞ በአገር ውስጥ አክራሪነትን እያስተባበረና እያስፋፋ ይገኛል፡፡

**3. *የሃይማኖት ትምህርት ተቋማት ውስጥ አክራሪና ጽንፈኛ ትምህርቶች እንዲስፋፉ የሚያደርገውን ተጽዕኖ እንዲያቆም፤***

በአሁኑ ጊዜ እየተካሄደ የሚገኘው እንቅስቃሴ የተጀመረው በአወሊያ ኮሌጅ የሚገኙ ተማሪዎች የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በት/ቤቱ ውስጥ የአህባሽ አስተምህሮትን ለማስገባት የሚያደርገውን ሙከራ በመቃወም ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተቋሙ አመራር ቦርድ በሳዑዲ አረቢያ የሚገኘውና ጽንፈኝነትን በዓለም ዙሪያ ለሚያስፋፋው ዓለምአቀፍ እስላማዊ ዕርዳታ ድርጅት (IIRO) በመባል በሚታወቀው ቡድን ሥር እንዲሆን ህወሃት የሚያደርገውን ተጽዕኖ እንዲያቆም በመቃወም ነበር፡፡ ይህንን ተቃውሞ የቀጠሉት ተማሪዎች **"የአወሊያ ንቅናቄ"** በመባል የአህባሽነትን ትምህርት በጽኑ በመቃወማቸው ለእስር ተዳርገዋል፤ በመቻቻል የሚያምኑ ሙስሊም መምህራንም ከሥራቸው ተባርረዋል፣ ታስረዋል፤ መስጂዶችና ሌሎች የትምህርት ተቋማትም ተዘግተዋል፡፡ **"የአወሊያ ንቅናቄ"** ግን አሁንም የሃይማኖት ነጻነት እንዲሰፍን እንዲሁም የሃይማኖትና መንግሥት ልዩነት እንዲከበር፤ ሃሳብን በነጻ የመስጠትና የመሰባሰብ መብት እንዲኖር ከመጠየቅ አላቋረጡም፡፡

ጥያቄዎቹ ጠቅለል ሲደረጉ ***የመጅሊሱ መሪዎች በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ይመረጡ፤ የአህባሽ አስተምሮት እንዲስፋፋ በአገዛዙ በኩል በግልጽ የሚደረገው ግፊት ይቁም እንዲሁም በአወሊያ የተጀመረው የሙስሊሞች ተቃውሞና ጥያቄ የመላው ኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄ በመሆኑ ህጋዊነት የሌለው መጅሊስ እጁን ከአወሊያ ላይ ያንሳ፤ አወሊያም በነጻነት ራሱን ያስተዳድር የሚሉ ናቸው፡፡*** ከህወሃት/ኢህአዴግ ደጋፊዎች በስተቀር ይህ በእውነቱ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጥያቄዎች አይደሉምን?

**እነዚህ የመብት ጥያቄዎች የሙስሊም ወንድሞችና እህቶቻችን ብቻ ሳይሆኑ የሁላችንም በመሆኑ የጋራ ንቅናቄያችን ለሰብዓዊነት ከመቆሙ አኳያ የሚደግፋቸው ሲሆን ሌሎችም ኢትዮጵያውያን በዚህ ዙሪያ አብረው እንዲቆሙ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡**

ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ የአቶ መለስ አገዛዝ በአገራችን ላይ ለዘመናት ተከባብሮና ተፋቅሮ የኖረውን ክርስቲያንና ሙስሊም በመከፋፈል አንዱ ሌላውን በዓይነቁራኛ እንዲመለከት፤ አንዱ ሌላውን "አሸባሪ" እንዲለው ከማድረግ አልፎ ደም እስከመፋሰስ እንዲደርስ አድርጎታል፡፡ **ይህ ኢትዮጵያውያንን በዘር በመከፋፈል ሲያናቁር የኖረው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ "በቃህ" ሊባል ይገባዋል፡፡ በመካከላችን ያለውን የጥልና የመከፋፈል ግድግዳ አፍርሰን የሌላው ነጻነት ማጣት የእኛ መሆኑን በመገንዘብ እጅለእጅ ተያይዘን ብሔራዊ ዕርቅ በማድረግ በህብረት የምንቆምበት ጊዜ አሁን ነው፡፡**

በመሠረቱ ሃይማኖቶች መከባበርንና ሰላምን እንደሚሰብኩ እሙን ነው፡፡ ምንም እንኳን በየሃይማኖቱ የተለያዩ አመለካከቶች ቢኖሩም "ሌላውን ጥላ" የሚል ወይም "ለሌላው መጥፎ ሁን" በማለት የሚያስተምር ሃይማኖት አለ ለማለት ያስቸግራል፡፡ መጠነኛ ልዩነቶች ቢኖሩ እንኳን እነዚህን ልዩነቶች በማስፋትና ሕዝብን ከሕዝብ ጋር በማጋጨት ለራሳቸው የሥልጣን መጠቀሚያ የሚያደርጉ እንዳሉ ይኸው በገሃድ የምናየው ነው፡፡ ሆኖም ቅዱስ ቁርአን እንደሚለው ***"መልካም መታደግን የሚታደግ ሰው ለእርሱ ከርስዋ ዕድል ይኖረዋል፤ መጥፎ መታደግንም የሚታደግ ሰው ለእርሱ ከርስዋ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡ በሰላምታ በተከበራችሁም ጊዜ ከርሷ ይበልጥ ባማረ (ሰላምታ) አክብሩ፤ ወይም (እርሷኑ) መልሷት፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ተቆጣጣሪ ነውና፡፡"*** አል-ኒሳእ 5፤85፣86 እንዲሁም በሌላ ቦታ ላይ ***"በአላህ መንገድ በተጓዛችሁ ጊዜ አስረግጡ፤ ሰላምታን ወደናንተ ላቀረበ ሰው የቅርቢቱን ህይወት ጥቅም የምትፈልጉ ሆናችሁ "ምዕመን አይደለህም" አትበሉ፤ . . . ከዚህ በፊት እንደዚሁ ነበራችሁ፤ አላህም በእናንተ ላይ ለገሰ፤ ስለዚህ አስተውሉ፤ አላህ በምትሰሩት ሁሉ ውስጥ ዓዋቂ ነውና፡፡"*** አል-ኒሳእ 5፤94 መጽሐፍ ቅዱስም እንዲሁ ***"የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና። … በሰማያት ያለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥… እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም በዚህ ይጠቃለላል።"*** ማቲዎስ 5፡9፤ 5፡44፤ 7፡12

**ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን ጎረቤትና ወዳጅ በመሆን በምንኖርበት መሬት ላይ ኑሮን የምንካፈል ብቻ ሳንሆን ከአያት ቅድመ አያታችን ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣ አንድ ደም የተቀዳን የአንድ ቤተሰብ አባላት ነን፡፡ "ኢትዮጵያዊነታችንም ለሙሐመድ ለሙሴና ለክርስቶስ የሚጨሰው ዕጣን በእርገት መጥቆ የሚደባለቅበት እምነት ነው፡፡"** ይህ እምነታችን ከገዢዎች የሚለገስ ወይም የሚከለከል ሳይሆን ፈጣሪ ስንወለድ ጀምሮ የሰጠን የራሳችን የሆነ ማንም ሊደፍረው የማይችል መብታችን ነው፡፡ በአበሻ ምድር ተቻችሎ መኖር ከጥንት ጀምሮ የኖረና ወደፊትም መቀጠል ያለበት ነው፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ሰአወ) ተከታዮቻቸው ወደ ኢትዮጵያ ሄደው ሰላምንና ዕረፍትን እንዲያገኙ ሲመክሩ ይህንን ያሉት በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች እንዳሉ ሳያውቁ ቀርተው ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ይልቁንም ተቻችሎና ተከባብሮ ለመኖር የአበሻ አገር ምቹ እንደሆነ አስቀድመው ስላወቁ ነው እንጂ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኖረው ይህ መከባበር ምንም እንኳን በተለያየ ጊዜ በገዢዎች ተጽዕኖ ሥር በመውደቁ አንዴ ሲጠብቅ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲላላ ቢሄድም እስካሁን ሳይበጠስ እኛ ልጆቻቸው ዘንድ ደርሷል፡፡

በፊታችን የሁላችንም የሆነችውን "አዲሲቷን ኢትዮጵያ" የመገንባት ኃላፊነት ወድቆብናል፡፡ "ይህችን አዲስ ኢትዮጵያ እንዴት ነው የምንገነባት?" የሚለው ከፊታችን የተደቀነ ጥያቄ አለ፡፡ በጭፍን ብሔረተኝነት? በክርስቲያን ወግ አጥባቂነት? በእስልምና አክራሪነት? በጨቋኝ ፊውዳላዊ አስተሳሰብ? በጠባብ ጎሰኝነት? በዘር የበላይነት? ሌሎችን "እነርሱ" ወይም "ከእኛ ጋር ያልሆኑ" ብሎ በመጥራት? . . . ነገሮችን በእውነትና በቅንነት መነጋገር መቻል አለብን፡፡ በሁላችንም ዘንድ የተፈጠረ መፈራራትና መለያየት አለ፡፡ "ከእኛ ወገን" ያልሆነውን በጥርጣሬ የመመልከት አካሄድ በግልጽ ይታያል፡፡ ይህ መቆም አለበት!! አገር እየወደመ፣ ሃይማኖት እየረከሰ፣ ዲን በርካሽ እየተሸጠ፣ መስጂድና ገዳማት እየፈረሱ ለመለያየትና የጎሪጥ ለመተያየት ጊዜ ሊኖረን አይገባም፡፡ አዲሲቷን ኢትዮጵያ የምንገነባው በውሸት፣ በጽንፈኝነት፣ በአስመሳይነት፣ በመፈራራት፣ በማጭበርበር፣ አንዱን ከሌላው የበለጠ ወንጀለኛ በማድረግ ሳይሆን ከሁሉ በፊት ሰብዓዊነትን በማስቀደም ብቻ ነው፡፡

ስለሆነም የጋራ ንቅናቄያችን በዋንኛነት የሃይማኖት መሪዎች ውይይት የሚጀምሩበትንና ለብሔራዊ ዕርቅ ትብብር የሚያደርጉበት ወሳኝ ጊዜ ላይ እንደሚገኙ ያምናል፡፡ ከዚህ በፊት ስናደርገው እንደቆየነው ሁሉ በአሁኑ ጊዜ በተለየ መልኩ ይህ ሃሳብ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ እያመቻቸን ይገኛል፡፡ ለዚህ የተቀደሰ ሃሳብ መቆም ልመናና ጥሪ የሚያሻው ሳይሆን እያንዳንዱ የሃይማኖት መሪ "እኔ ዝግጁ ነኝ" በማለት በአፋጣኝ ምላሽ የሚሰጥበት ሊሆን ይገባል፡፡ እንዲህ ያለውን ዕድል እየናቁና ለከሌሎች ጋር ተባብሮ ከመስራት ገሸሽ እያሉ "መብቴ አልተጠበቀም፤ ሃይማኖቴ አደጋ ላይ ወድቋል" ማለት የማያዋጣ አሰራር ብቻ ሳይሆን በታሪክ ጭምር የሚያስጠይቅ ነው፡፡



በቶሮንቶ የተካሄደው ሰልፍ የአዲሲቷ ኢትዮጵያን መልክ ያሳየ ብልጭታ ነው

በቅርቡ በቶሮንቶ ካናዳ የወንጌላዊት ቤ/ክ ፓስተር፣ የሙስሊም ኢማምና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ ካህናት በኅብረት በመሆን አንዱ ለሁሉም፤ ሁሉም ለአንዱ በመቆም የጋራ ኅብረታቸውን እንዳሳዩት ሁሉ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር በመቀጠል በሌሎችም ዘንድ በስፋት እየተለመደ መምጣት እንዳለበት የጋራ ንቅናቄያችን ያሳስባል፡፡

በአገራችን ላይ ያለውን ሰቆቃና መከራ ለእኛው ለራሳችን መንገር የወቅቱ ጥያቄ አይደለም፡፡ በየእምነታችንም "ፈጣሪ ሆይ እስከመቼ ይሆን በመከራ የምንኖር?" ብለን ብንጠይቀው "እርስ በርሳችሁ መዋደድ እስክትችሉ" የሚል እንደሚሆን ሁላችንም እናውቀዋለን፡፡ ይህ የእኛ ትውልድ አገርን፣ ቅርስን፣ እምነትን፣ ዲንን እንዲሁም ኢትዮጵያዊነትን የማዳን ኃላፊነት ወድቆብናል፡፡ ተገቢውን ምላሽ መስጠት እንድንችል ፈጣሪ ይርዳን፡፡

**ስብሐት ለአብ፣ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ!**
**አላሁ አክበር!**



ኦባንግ ሜቶ
ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ
ዋና ዳይሬክተር

***********************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

